የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ መጋቢት ፰ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16[th] Year No. 16
ADDIS ABABA 17[th] March 2010

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፸፭/፪ሺ፪
የገነት ሆቴል ድርጅት ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........ ገፅ ፭ሺ፪፻፲፫

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፭/፪ሺ፪

**የገነት ሆቴል ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞ ክራሲያዊ ሪፐብሊሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/ ፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርእስ**

ይህ ደንብ "የገነት ሆቴል ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፭/፪ሺ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **መቋቋም**

፩. የገነት ሆቴል ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፫. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ማዕከል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መስሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **ዓላማ**

የድርጅቱ ዓላማ የሆቴልና ከሆቴል ጋር የተያያዙ የአገልግሎት ሥራዎችን መሥራትና ለሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ በሞዴል ሆቴልነት ማገልገል ይሆናል፡፡

ያንዱዋጋ
Unit Price 2.45

CONTENTS

Regulation No. 175/2009
Genet Hotel Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation ..........Page 5213

Council of Ministers Regulation No. 175/2002

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF GENET HOTEL ENTERPRISE**

This Regulations is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the “Genet Hotel Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 175/2009.”

2. **Establishment**

1. The Genet Hotel Enterprise (hereinafter the “Enterprise”) is hereby established as a public enterprise.
2. The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. **Supervising Authority**

The Catering and Tourism Training Center shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. **Head office**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. **Purpose**

The purpose of the Enterprise shall be to engage in the business of hotel and related services and serve as a model hotel for training in catering and tourism.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፮. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፵ሚሊዮን (አርባ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፱ ሚሊዮን ፱፻፳፮ሺ ፯፻፲፫(ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ስድስት ሺ ሰባት መቶ አሥራ ሦስት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

የገነት ሆቴልን የሚመለከቱ የራስ ሆቴሎች ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡-

፲. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ደህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፰ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

6. **<u>Capital</u>**

The authorized capital of the Enterprise is Birr 40,000,000,.00 (Forty Million Birr) of which Birr 9,926,713.00 (Nine Million Nine Hundred Twenty Six Thousand Seven Hundred Thirteen Birr) is paid up in cash and in kind.

7. **<u>Liability</u>**

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. **<u>Duration of the Enterprise</u>**

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. **<u>Transfer of Rights and Obligations</u>**

The rights and obligations of Ras Hotels Enterprise relating to Genet Hotel are hereby transferred to the Enterprise.

10. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 17th day of March 2010.

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት